

# የሙስና ወንጀሎች መሠረታዊና ሥነ ሥርዓታዊ ሕጎች በኢትዮጵያ

FIGHT CORRUPTION

# የአሰልጣኝ አጭር መረጃ

ስም - ገብረእግዚአብሔር ወልደገብሪኤል

ተቋም - የፍትሕ ሚኒስቴር የሙስና ወንጀሎች ዳይሬክቶሬት ጀነራል

ምክትል ረዳት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ

የትምህርት ደረጃ - በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪ (LL.B)፤ በዓለም አቀፍ ሕግ- ማስተርስ ዲግሪ (LL.M)

የስራ ልምድ - 10 ዓመት

# ይዘት/Outline

**ይህ ሥልጠና ክፍል አራት መሰረታዊ ክፍሎች ይዟል።**

- ክፍል 1፡-  ስለ ሙስና ጽንሰ ሐሳብ በጠቅላላው
- ክፍል 2፡- ዓለም አቀፋዊና ብሔራዊ የጸረ ሙስና ሕጎች
- ክፍል 3፡- ከባድ ሙስና/Grand Corruption
- ክፍል 4፡- ልዩ የምርመራ ዘዴዎች

# የስልጠናዉ አሰጣጥ ዘዴ

ሥልጠናዉ በሚከተሉት ሁኔታ የሚከናወን ይሆናል፡፡

- በአሰልጣኝ የሚደረግ ገለፃ፣
- የሠልጣኞች ተሳትፎ፣
- የመወያያ ነጥቦች (ጥያቄዎች) በግል/በጋራ መስራት፣ ማቅረብ
- አከራካሪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ማተኮር፡፡

# የሥልጠናዉ ግብ

- **ሠልጣኞች፡-**
  - ❖የሙስና ወንጀሎች ዙሪያ በቂ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፣
  - ❖የሙስና ወንጀሎች ከሌሎች መደበኛ ወንጀሎች ያላቸው ልዩነት ይገነዘባሉ።
  - ❖አከራካሪ በሆኑ ጉዳዮች በጋራ ውይይት ተቀራራቢ አቋም ለመያዝ ይረዳቸዋል
  - ❖በሙስና እንዲጠየቁና እንዳይጠየቁ የተደረጉ አካላትን ከነምክንያቱ መለየት ይችላሉ፣
  - ❖የሙስና ወንጀል ምርመራና ክስ የሚመራበትን ሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ ይዘትናና አተገባበር ግንዛቤ ይኖራቸዋል፣

# ክፍል አንድ

## ስለ ሙስና ወንጀል በጠቅላላ

“Corruption is present in all countries, rich and poor, North and South. ...It robs societies of schools, hospitals and other vital services, drives away foreign investment and strips nations of their natural resources. It undermines the rule of law and abets crimes such as the illicit trafficking of people, drugs and arms. …the cost of corruption is at least £2.6 trillion [and] businesses and individuals pay more than $1 trillion in bribes each year.”

(António Guterres, United Nations Secretary-General, 9 December 2018)

# ሙስና ምንድን ነው?

# ስለ ሙስና/Corruption ትርጉም

- የእንግሊዘኛው ቃሉ "corruptus“ ወይም Corruptio ከሚለው የላቲን ቃል የተወሰደ ነው። “rotten, decayed, corrupted” የሚለውን ይተካል።
- ሙስና የሚለው የአማርኛ ቃል መሰረቱ ግዕዝ ሆኖ ትርጉሙም ጥፋት፣ መበስበስ፣ መፍረስ፣ ብልሹነት፣ ንቅዘት፣ በመጥፎ ድርጊት መተዳደር፣ ምግባረ ንቅዘት ማለት ነው

# የቀጠለ...

- ❖ሙስና አደራን አለመጠበቅ፣ እምነት ማጉደል ወይም አለመታመን፣ በምልጃና በአድሎ ውሳኔን ወይም ፍትህን ማዛባት ነው፡፡ (**Black's Law Dictionary**)
- ❖ከሕግ አንጻር ሙስና ለሚለው ቃል ትርጉም መስጠት አስቸጋሪ ነው፣
- ❖ሕጋዊ ትርጉም መስጠቱ ለምን አስቸጋሪ ሆነ?
- ✓ፅንሰ ሃሳቡ ሀይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ህጋዊ መሆኑ
- ✓አፈፃፀሙ ከአገር፣ ከቦታ፣ እና ከባህል አንፃር የተለያየ መሆኑ
- ❖የፀረ-ሙስና ስምምነቶች ትርጉም ከመስጠት የተቆጠቡ ናቸው፣
- ❖የሙስና ወንጀሎች **አዋጅ ቁ. 881/2007** አንቀፅ 4(2) ቀጥታ ትርጉም ከመስጠት ይልቅ የሙስና ድርጊቶችን ያብራራል፡፡

## የቀጠለ…

ሆኖም እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል፡፡

- የሕዝብን ጥቅምና ፍላጎት ለግል ጥቅም ማዋል፣
- በመንግሥትና የሕዝብ ሀብትና ንብረት ላይ ስርቆት፣ ዝርፊያ እና ማጭበርበር መፈፀም፤
- ህግና ስርዓትን በመጣስ በጉቦ፣ በዝምድና፣ በትዉዉቅ፣ በፖለቲካ ወገንተኝነት፣ በጎሰኝነት፣ በሀይማኖት ትስስር ላይ ተመርኩዞ አድሎ መፈፀም፣ ፍትሕን ማጓደል እና ሥልጣንና ሀላፊነትን አላግባብ መጠቀም፣
- **ማንኛውም የሕዝብ ሥልጣን/እምነት ይኑርህ እሱን ለግል ጥቅም አታውለው ወይም አታጉድል፡፡**

# የቀጠለ...

- ማጭበርበር
- ጉቦኝነት (Bribery)
- ማስገደድ (Extortion)፤
- ሥልጣንን አለአግባብ መገልገል (Abuse of Power)
- ማዳላት (Favouritism) ለቅርብ ቤተሰብ በማዳላት (Nepotism)፤ እና ለቅርብ ጓደኛ ማዳላት (Cronyism)፤
- በሥልጣን መነገድ
- ሀሰተኛ ሰነዶችን ማዘጋጀትና መገልገል፣ ማጥፋት
- ምዝበራ (Embezzlement)

የቀጠለ...

# (Transparency International)

# 'Abuse of entrusted power for private gain.'

(ሙስና የተሰጠ ሥልጣንን ለግል ጥቅም ሲባል አላግባብ መገልገል ነው)

- ) በዚህ ትርጉም መሰረት ሦስት መሰረታዊ ዋልታዎች እናገኛለን።

# የሙስና ወንጀል ዋልታዎች



ሥልጣን/Power

መዳረሻ ዕድል/Access

ሞኖፖሊ/Monopoly

ጥሰት/Violation

ጥቅም/ጉዳት{Gain/Harm

የቀጠለ...

ሙስና

ሞኖፖሊ + ሰፊ ፍቅደ ሥልጣን —

ታማኝነት — ግልጽነት — ተጠያቂነት

# የሙስና ወንጀሎች ዓይነት

1) ከፈጻሚዎች አንጻር የሙስና ክፍፍል

✓ፖለቲካዊ ሙስና (Political Corruption):-

- ከፍተኛ ባለሥልጣናትና ፖለቲከኞች ለምሳሌ  የሀገር መሪዎችና ሚኒስትሮች፣ ከፍተኛ ሃላፊነት ያላቸው ሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች ወዘተ የሚተውኑበት ነው፡፡
- በፖሊሲዎች፣ በሕጎችና በደንቦች አወጣጥ፣ የመንግሥት/የሕዝብ ሀብትና በሚመድቡበት/ሚያከፋፍሉበት ጊዜ ፖሊሲዎችን፣ ተቋማትንና የሕግ ሥርዓትን በማጣመም...

2) ቢሮክራሲያዊ ሙስና (Bureaucratic Corruption)

የመንግሥት ፖሊሲዎችን በመተግበር ሂደት ላይ በመንግሥት እና የሕዝባዊ ድርጅት ሰራተኞች የሚፈጸም ነው፡፡

- ይህ ወንጀል በግለሰብ ደረጃ አነስተኛ ገንዘቦችና ጥቅሞች የሚገኝበት ዝቅተኛ (Petty Corruption) ወይም አስተዳደራዊ (Administrative Corruption) የሙስና ወንጀል  ነው፡፡

# ከጉዳት አንጻር የሙስና ክፍፍል

1) **ቀላል** **(Petty Corruption)**

- መጠኑ አነስተኛ የሆነ ገንዘብ አላግባብ የሚገኝበት ነው፣
- መለስተኛ እና ዝቅተኛ ደረጃ ባላቸው የሚፈፀም ነዉ፣
- ህዝቡን የሚያማርር፣ ቶሎ የሚታወቅ በቀላሉ ትኩረት የሚያገኝ ነው

2) **ከባድ** **(Grand Corruption)**

- ከፍ ባሉ ባለስልጣኖች ወይም ፖለቲከኞች የሚፈፀም ነው፡፡
- ከፍተኛ ገንዘብ የሚመዘበርበት፣
- በትላልቅ የመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች (መንገድ፣ የግድብ፣ የባቡር ፣ የቴሌኮም ወዘተ ግንባታዎች)፣
- ከፍተኛ ገንዘብን የሚያንቀሳቅሱ (ገቢዎች፣ ጉምሩክ፣ ባንኮች ፣ ኢንሹራንስ ወዘተ) እንዲሁም
- ምስጢራዊ በሆኑ ከፍተኛ የገንዘብ እንቅስቃሴ ባላቸው የደህንነት እና የመከላከያና ተመሳሳይ መስሪያ ቤቶች የሚፈጸም የሙስና አይነት ነው፡፡

# የቀጠለ…

## 3) **መንግሥታዊ/ሲስተሚክ ሙስና (state capture) ፡-**

- በሕግ አወጣጥ፣ በምርጫ አፈጻጸም ሽፋን የሚፈፀም ነዉ፣
- ቢሮክራሲውን የአንድ የፖለቲካ አጀንዳ መጠቀሚያ በማድረግም ይገለጻል፡፡
- የመንግሥት ሥርዓት መዳከምና የሙስና ወንጀል ሀይሎች የመንግሥትን መዋቅር ከሞላ ጎደል ተቆጣጥረው የሚገኙበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው፡፡
- ሙስና እንደነውር የማይታይበት ነዉ፣
- ሙስናን መዋጋት እንደሞኝነት እና አላዋቂነት የሚታይበት ነው፡፡

# የሙስና ወንጀሎች መነሻ ምክንያቶች

- በሕንድ ሐገር -“የመንግሥት ገቢ የሚሰበስብ ባለሥልጣን፣ ማር የፈሰሰበት ምላስ ነው፤”

በኢትዮጵያም ተከታዮቹ አባባሎች ይነገራሉ

- “ተሹሞ የማይበላ፣ ተጥዶ የማይፈላ የለም፤”
- “ሲሾም ያልበላ፣ ሲሻር ይቆጨዋል፤”
- “አገር ሲዘረፍ፣ አብረህ ዝረፍ”

# የሙስና ወንጀሎች መነሻ ምክንያቶች



# የቀጠለ...

- በትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል በ2023 ሪፖርት መሰረት ዓለም ላይ ካሉት 180 ሀገራት ዉስጥ ፡-
  - ✓ዝቅተኛ ሙስና ያለባት ሀገር ዴንማርክ (1ኛ ደረጃ)
  - ✓ከፍተኛ ሙስና ያለባት ሀገር ሶማሊያ ናት (180ኛ ደረጃ) ፡፡
- ኢትዮጵያ 98ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፣ የደረጃ መውረድና መውጣት ይታያል፣

| Year | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | 2023 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Rank | 108 | 107 | 114 | 96 | 94 | 87 | 94 | 98 |



# የመወያያ ጥያቄ




የሙስና ወንጀል ከሌሎች ነባር ከሚባሉ
የወንጀል አይነቶችን በምን ይለያል ?



ልዩ ባህሪዉን ማወቅስ ምን
ጥቅም አለዉ?

# የሙስና ወንጀሎች ልዩ ባህሪያት




- ውስብስብ



- የፈጻሚዎች አቅም



- እኩል ተጠያቂነት



- ቀጥተኛ ተጠቂ አለመኖር



- ድንበር ተሻጋሪነት



- ንብረትን ማጠብና ሀብትን ማሸሸ

# ሙስና እና መዘዙ



# የቀጠለ…

- ድህነት
- የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት
- የዲሞክራሲ መዳከም
- ኢኮኖሚያዊ እድገትንና ልማትን ማዳከም
- የአካባቢ ጥበቃን ማስተጓጎል
- የተደራጁና ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎችን ምንጭነት

# ክፍል ሁለት

## ዓለምአቀፍና ብሔራዊ ሕግጋትን አጭር ዳሰሳ

# ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አጭር ዳሰሳ

- የተመድ ፀረ ሙስና ኮንቬንሽን (UNCAC) ጥቅምት 31 ቀን 2003 ዓ.ም የወጣ ነው፤ 8 ምዕራፎችና 71 አንቀጾች ይዟል ( 15-25)
- ስምምነቱ ሀገራት፡-
  - ሙስናን እንዲከላከሉ፤ በወንጀልነት እንዲደነግጉ
  - ትብብር እንዲያደርጉ፤የተመዘበረ ሀብት እንዲያስመልሱ ግዴታ ይጣላል፣
  - የማፑቶ ኮንቬንሽን ሐምሌ 11 ቀን 2003 የወጣ ተመሳሳይ ግዴታዎችን ይጥላል፡፡
  - የተመድ የተደራጁ ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎችን ለመከላከል የተደረገ ስምምነት፣እ.ኤ.አ ጥቅምት 15 ቀን 2000 ዓ.ም
- አገራችንም እነዚህን ኮንቬንሽኖች ተቀብላ በተከታታይ በአዋጅ ቁጥር 544/99፣ 545/99 እና አዋጅ ቁጥር 526/1999 አፅድቃለች፣

# የጸረ ሙስና ሕጎች በኢትዮጵያ ታሪካዊ ዳራ

- ➢በርካታ የፀረ ሙስና ሕጎች በማዉጣት በስራ ላይ አዉላለች፡፡
  - ✓የ1949 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ
  - ✓ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ (አዋጅ ቁጥር 8/1967)
  - ✓አዋጅ ቁጥር 214/74 ተካተዉ ነበር፣
- ➢የሙስና ወንጀል መገለጫ የሆኑ ተግባራት በወንጀልነት ተደንግገዉ ነበር፡፡

  ለምሳሌ፡-
  - ✓በሥልጣን አላአግባብ መገልገል፣
  - ✓በስልጣን ስለመነገድ፣
  - ✓ጉቦ መስጠትና መቀበል፣
  - ✓እምነት ማጉደል

# የቀጠለ…

- ➢ **ይሁንና፡-**
  - ▪ተበታትነው የሚገኙ፤
  - ▪ሙስና ድንጋጌዎች የትኞቹ እንደሆኑ የማያሳይ
  - ▪ሕጋዊ የሙስና ትርጓሜ ያልሰጡ ናቸው፡፡
- ➢በዚህ ምክንያት አዋጅ ቁጥር 236/93 ሊወጣ ችሏል፣
  - ❖ ልዩ ሥነሥርዓትና የማስረጃ ሕግ ደንቦችን ይዟል
  - ❖አዋጁ ለመጀመሪያ ጊዜ የሙስና ትርጓሜ ያስቀመጠ ነዉ፡፡

# የቀጠለ…

*“መንግስት ወይም ከሕዝብ አገልግሎት ወይም ከሕዝብ ጥቅም ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ማናቸዉም ወንጀል ሆኖ የተመደበበትን የመንግስት ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራ ያለአግባብ በመጠቀም ለራስ ወይም ለሌላ ሰዉ ወይም ለቡድን ጥቅም መጠየቅ፣ የተስፋ ቃል መቀበል ወይም ማግኘት ወይም ሌላዉን ሰዉ መጉዳት ሲሆን መደለያ መቀበልን፣ጉቦን፣ የማይገባ ጥቅም መቀበልን፣ በሥልጣን መነገድን፣ በሥልጣን ያለአግባብ መገልገልን፣የመንግሥት ስራ ወይም የሕዝብ አገልግሎት ስራን ለግል ጥቅም በሚያመቾ አኳኋን መምራትን፣በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም መዉሰድና መሰወርን፣በመንግሥት ስራ ላይ ሆኖ በማስገደድ መጠቀምን ፣ሚስጥር ማባከንን እና የመሰሰሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል።”* **(አንቀጽ 2 (1)**

የቀጠለ…

- በአዋጁ የተቀመጠዉ ትርጉም፡-
  - የመንግሥትን ሥልጣን ወይም ሀላፊነት ለግል ጥቅም ማዋል የሚለዉን ለሙስና ትርጉም መሠረት ያደረገ ነዉ፡፡
- **ይሁንና ሰፋፊ ችግሮች ነበሩበት፡-**
  - ነባር የሚባሉት ጉቦ መስጠትና ማቀባበልን፣
  - አዳዲስ የሚከሰቱ ወንጀሎች በግልፅ አላካተተም፡፡
  - "….የመሳሳሉትን ሌሎች ይጨምራል" የሚለዉ ለይሆናል (አናሎጂ) የተጋለጠ ነበር፣
  - ወጥ ዉሳኔ እንዳይኖርና መቋጫ የሌለዉ የትርጉም ልዩነት እንዲፈጠር አድርጓል፡፡

# የቀጠለ…

- በአዋጅ ቁጥር 434/1997 እንዲሻሻል ተደርጓል፣
- ትርጓሜውም እንዲቀር ተደርጓል። በዚህም መሰረት የሙስና ወንጀል ማለት በኢፌዲሪ ወንጀል ሕግ የተመለከቱት ናቸው በማለት በአንቀጽ 2 (1) ላይ ደንግጓል።
- በ1996 የወንጀል ሕግ በተሻለ መልኩ ተደንግጎ ነበር፣
- በወንጀል ሕጉ አወቃቀር መሰረት፣
  - የሙስና ወንጀሎች የሚባሉት በግልፅ እንዲቀመጡ ፣
  - በአንድ አካባቢ እንዲሰባሰቡ ተደርጓል።
- በዚህ ሕግ ስለሙስና ወንጀል ቀጥተኛ ትርጉም ተቀምጦ አናገኝም፣

# የቀጠለ...

- ወንጀሉ በመንግሥት ሠራተኛ ወይም በማንኛውም ሰው ሊፈፀም የሚችል መሆኑን በአንቀፅ 404 (3) እና
- የሙስና ወንጀል ሊባሉ የሚችሉት የትኞቹ ድንጋጌዎች እንደሆኑ በሕጉ አንቀፅ 404 (4) ላይ ተመልክቷል፡፡
- የሙስና ወንጀል ተብለው የተለዩት 23 አንቀፆች ብቻ ናቸው፣
- እነዚህም፡-
    - በመንግስት ሠራተኛ የሚፈፀሙ (አንቀፅ 407-419)፣
    - ከመንግስት ሥራ ጋር በተያያዘ በሌሎች ሰዎች (አንቀፅ 427-431
    - በማንኛውም ሰው የሚፈጸሙ(አንቀፅ 379፣468፣684፣676(1) 696(ሀ)

በሚል የተቀመጡ ናቸዉ፡፡

**ይህም ሆኖ በወንጀል ሕጉ ላይ የተመለከቱት የሙስና ወንጀሎች ተሽረው በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ተጠቃልለዋል፡፡**

# አዋጅ ቁጥር 881/2007

- የሚከተሉት ምክንያቶች መነሻ ነበሩት (የአዋጁ መግቢያ)፣
  - ✓አሻሚ ድንጋጌዎችን ግልጽ ማድረግ በማስፈለጉ፤
  - ✓በግሉ ዘርፍ የሚፈፀም ሙስና የሚገዛ የሕግ ማዕቀፍ በማስፈለጉ፣
  - ✓በተመድና በአፍሪካ የፀረ ሙስና ኮንቬንሽን የተጣለዉን ግዴታ ለመወጣት፤
  - ✓አንድ ወጥ የሆነ አጠቃላይ ሕግ ራሱን በቻለ አዋጅ ማውጣት ማስፈለጉ ናቸው፡፡ (ከሙስና ተለዋዋጭ ባህሪ አንፃር)
  - ✓አዋጅ ቁጥር **882/2007** አንቀጽ **2(1)** የሙስና ወንጀል ማለት በአ/ቁ **881/2007** የተሰጠውን ትርጓሜ ይኖረዋል በማለት ያስቀምጣል፡፡
  - ✓ሆኖም በአ/ቁ. **881/2007** ስለ ሙስና ወንጀል በቀጥታ የተሰጠ ትርጉም የለም፣ የሙስና ወንጀሎች የተባሉትን ግን በዝርዝር ያስቀምጣል፡፡

# የቀጠለ...

- ‘መርሕ’ በሚል ርዕስ በአንቀጽ 4 (2) ስር የሙስና ባሕሪና መገለጫ አስቀምጧል፡፡

- ✓ *ጉቦ መቀበል*
- ✓ *ሥልጣን ያለአግባብ መገልገል*
- ✓ *ጉቦ መስጠት -(የእንግሊዘኛው ቅጇ ማንኛውም ሰው)*
- ✓ *የማይገባ ጥቅም መስጠት- (የእንግሊዘኛው ቅጇ ማንኛውም ሰው)*
- ✓ *የማይገባ ጥቅም መቀበል*

# የተፈጻሚነት ወሰን


ሰራተኞች
የመንግሥት ሰራተኛ
የሕዝባዊ ድርጅት ሰራተኞች
ጊዜያዊና ተለማማጅ ሰራተኞች የስራ አመራር ቦርድ
ማንኛውም ሰው
ልዩ ሃላፊነት ያለባቸው ሰዎች
በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች

- **ሰራተኞች**

- የመንግሥት ሰራተኛ ማለት በመንግሥት ወይም በመንግሥት የልማት ድርጅት፣ የሕዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ማለት ደግሞ በሕዝባዊ ድርጅት ተቀጥረው፣ ተሹመው ወይም ተመርጠው የሚሰሩ ናቸው።
- በክፍያ ወይም ያለክፍያ፣ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ሊሆን ይችላል

# የቀጠለ…

- **ሕዝባዊ ድርጅት**” ማለት አዋጁ በአንቀጽ 2(4) ፡-
  - ✓ ከአባላት ወይም
  - ✓ ከሕዝብ ወይም
  - ✓ ለሕዝባዊ አገልግሎት ታስቦ የተሰበሰበ ገንዘብ፣ ንብረት ወይም ሌላ ሀብትን የሚያስተዳድር አካልን ሲሆን፣“ *(በበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የሚተዳደር)*
  - ✓ አግባብነት ያለው ኩባንያን የሚያካትት የግል ዘርፍ ነዉ፡፡
- አግባብነት ያለው ኩባንያን ማለት (አንቀጽ 2/6)፡-
  - ✓በሕዝባዊ ድርጅት የተቋቋመ ሃላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ ሲሆን
  - ✓እንደዚህ ባሉ ኩባንያ የሚመሰረቱ የሽርክና ማህበራትን ይጨምራል፣

# የቀጠለ...

- ❑ በህዝባዊ ድርጅት የሚተዳደረዉ ሃብት (ረቂቅ አዋጅ አጭር ማብራሪያ )
  - ✓ከአባላት፡- በአባልነት መዋጮ ወይም በአክስዮን ክፍያ የተሰበሰበ ወይም
  - ✓ከሕዝብ፡- በቋጠባ፣ በመድን ዋስትና አረቦን፣ በቴሌቶን ወዘተ የተሰበሰበ ወይም
  - ✓ለሕዝባዊ አገልግሎት እንዲውል የተሰበሰበ ገንዘብ ወይም ንብረት ወይም ሀብት እንደሆነ ይገልጻል፣
- ❑ ከአባላት ወይም ከሕዝብ በተሰበሰበ ሀብት ከሚያስተዳድሩ የግል ድርጅቶች መካከል፡-
  - ✓የአክስዮን ማህበራት፣
  - ✓ዩኒየኖችን ጨምሮ የህብረት ስራ ማህበራት፣ በሕብረት ሥራ ማሕበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009
  - ✓የልማት ማህበራት፣
  - ✓የሙያና የብዙሀን ማህበራት፣
  - ✓ የስፖርት ፌደሬሽኖች/ማሕበራት፣
  - ✓የሀይማኖት ድርጅቶች፣
  - ✓የፖለቲካ ድርጅቶች፣
  - ✓ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣
  - ✓አነስተኛና ጥቃቅን ማህበራት፣
  - ✓እድሮችና መሰል **ባሕላዊ ማሕበራት** ወዘተ..የሚካተቱ መሆኑን ማየት ይቻላል፣

# የቀጠለ…

- ❑በቁጠባ ወይም በመድን ዋስትና አረቦን መልክ የተሰባበሰ ሀብት ከሚያስተዳድሩ ውስጥ፡-
  - ✓ባንኮች፣
  - ✓የኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣
  - ✓የሀዋላ አስተላለፊ ኩባንያዎች ይጠቀሳሉ፡፡
- ❑ ለሕዝባዊ አገልግሎት እንዲውል ታስቦ የተሰበሰበ ሀብት የሚባለዉ ፡-
  - ➢የተወሰነ የህብረተሰብ ክፍልን ወይም ህብረተሰቡን በአጠቃላይ፡-
    - ✓ ለመርዳት/ለመደገፍ
    - ✓ለማበረታታት ወይም
    - ✓ለማልማት ታስቦ የሚሰበሰበ እና በበጎ አድራጎት ወይም በማህበራት የሚተዳደር ሀብት ነዉ፣
- ❑ የበጎ አድራጎት ማለት (አንቀጽ 2/8) ፡-
  - ✓ አግባብ ባለዉ ሕግ የተመዘገበ፣
  - ✓ ለበጎ አድራጎት አላማ የተቋቋመ፣
  - ✓ የሕዝብ ጥቅም ያለው ተቋም ነዉ፣

ሁሉንም ዓይነት የንግድ
ማሕበራት በአ/ቁ.
881/2007 መሰረት
በሕዝበዊ ድርጅት
ትርጓሜ ውስጥ
ይሸፈናሉን?

# የቀጠለ...

- የንግድ ማህበራት በቀድሞዉ የንግድ ህግ 6 ሲሆኑ (አንቀጽ 212) ፣
- በአዲሱ ንግድ ህጉ የተፈቀዱት ደግሞ 7 ናቸዉ (አንቀጽ **174)፣**
  - የኅብረት ሽርክና ማኅበር፣
  - ሁለት ዓይነት ኃላፊነት ያለበት የሽርክና ማኅበር፣
  - ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር፣
  - የእሽሙር ማኅበር፣
  - (ሃላፊነቱ የተወሰነ) የአክሲዮን ማሕበር-የሕዝብ ኩባንያ
  - ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር፣
  - ባለአንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር።
- ከነዚህ ዉስጥ የሕዝባዊ ድርጅት በተሰጠዉ ትርጉም የሚካተቱት የትኞቹ ናቸዉ?

# ልዩ ሃላፊነት ያላቸው ሰዎች/አካላት

- ይህን አገልግሎት ብቁ ላልሆነ ወይም ሊሰጠው ለማይገባ ሰው ከሰጡ በመንግስት እና በህብረተሰቡ ላይ የሚያደርሱት ጉዳት ከፍተኛ መሆኑ ግልፅ ነዉ፡፡
- ለምሳሌ የሚከተሉትን ማንሳት ይቻላል፡-
  - የመንጃ ፈቃድ
  - የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ
  - የሰዉ ጤንነት ማረጋገጫ
  - የትምህርት ደረጃ ማረጋገጫ የሚሰጡ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በዚህ አግባብ በሙስና ይጠየቃሉ፡፡
- **እነዚህ አካላት በሙስና እንዲጠየቁ ለምን ተደረገ?**

# የቀጠለ...

- በተጨማሪም
  - አስታራቂ ሽማግሌ፣
  - የግልግል ዳኞች፣
  - ንብረት ጠባቂ ወይም አጣሪዎች፣
  - በባለሥልጣን የተሾመ ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚዎች፣
  - በዳኝነትና በዳኝነት ነክ በሚታይ ጉዳይ አስተያየቱን ወይም የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥ ማንኛውም ልዩ አዋቂ ወይም ኤክስፐርት፣
  - ገቢና ወጪን ኦዲት የሚያደርግ ኦዲተር፣ ወይም
  - የግንባታ ጥራትን የሚያረጋግጥ መሃንዲስ፤

# *ማንኛውም ሰው*

- **ልዩ ተካፋይ**
  - ✓ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 33
  - ✓በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 4 (3) (ሀ) (ለ) እና አንቀጽ 4 (4)
  - ✓ ሰበር ሰሚ ችሎቱም በቅፅ 13፣ ሰ/መ/ቁ 60542 እና በሌሎች
- **ማንኛውም ሰው እንደሚጠየቅ ሕጉ ሲደነግግ፡-**

*"አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 4(1) "ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ **ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን የሙስና ባህርይ የሚያሟላ ወንጀል በፈጸመ ጊዜ ለወንጀሉ የተደነገጉት የቅጣት ድንጋጌዎች ይፈፀሙበታል።"*

- *ከአንቀጽ 23-30፣* ***{32(ሐ)?}*** *፣ 33*

# የቀጠለ...

- የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን በሀሰት ማዘጋጀትና መገልገል፤ (23)
- ሰነዶች ማጥፋት ወይም ጉዳት ማድረስ፤ (24)
- ጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠት፤ (25)
- ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ መስጠት፣(26)
- ማቀባበል፣ (27)
- በሌለው ሥልጣን መጠቀም፣ (28)
- በግል ተሰሚነት መነገድ፣ (29)
- ለምርጫ ዓላማ መደለያ መስጠት ወይም መቀበል (30) እንዲሁም **{ከባድ አታላይነት (32(ሐ)?}**
- በወንጀል የተገኘ ንብረት ወይም ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ (33)

# በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች

**በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች (legal persons)**

- ሰራተኞች
- ወኪሎች
- ለእነሱ ተጠሪ የሆኑ አካላት በሚፈፅሙት ጥፋት፣
- (በጉበ መስጠት፣ መኒ ላውንደሪንግ ብቻ)

# የቀጠለ...

**❑የወንጀል ሕግ አንቀጽ 90(3)**

- *እስከ አምስት ዓመት ቀላል እሥራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ብር አስር ሺ፤*
- *እስከ አምስት ዓመት ፅኑ እሥራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ብር ሃያ ሺ፤*
- *እስከ አስር ዓመት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ብር ሃምሳ ሺ፤*
- *ከአስር ዓመት በላይ ጽኑ እሥራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ 5 መቶ ሺህ መቀጮ ሊደርስ ይችላል።*

**❑አዋጅ ቁጥር 881/2007**

- በቀላል እስራት ለሚያስቀጣ ለእያንዳንዱ የቅጣት ዓመት ሃያ ሺህ ብር፤
- ከ5 ዓመት በታች ጽኑ እሥራት ለሚያስቀጣ ለእያንዳንዱ የቅጣት ዓመት 30 ሺህ ብር፤
- ከ5- 10 ዓመት ጽኑ እስራት ለሚያስቀጣ ለእያንዳንዱ የቅጣት ዓመት 50 ሺህ ብር፤
- ከአስር ዓመት በላይ ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ለእያንዳንዱ የቅጣት ዓመት

ለምሳሌ በመደበኛ ወንጀል 3 ዓመት ጽኑ እስራት የተቀጣ ድርጅት 20 ሺ ብር ሲቀጣ በጉቦ መስጠት ሲሆን ግን 3 X 30 ሺ= 90 ሺ

**ፍትሐዊ ነውን? ለምን?**

# አዋጁ የማይፈጸምባቸው የግል ዘርፎች

ሕዝባዊ ድርጅት ቢሆኑም የሚከተሉት በዚህ ትርጉም ውጪ ናቸው

- የሃይማኖት ድርጅትን፣
- የፖለቲካ ድርጅትን ፣
- የዓለም አቀፍ ድርጅትን፣
- ዕድርንና ተመሳሳይ ባህላዊ ወይም ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው ማህበራት

እነዚህ ድርጅቶች ከአዋጅ ቁጥር 881/2007 ውጪ ለምን ተደረጉ? ተገቢ ነው ብለው ያምናሉ?

**በሃይማኖት ተቋማት ስር የተቋቋመ የተራድኦና የበጎ አድራጎት ድርጅት?**

**አንቀጽ 2(9) እና ረቂቅ ሰነዶቹ**

# በግል ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚነት የሌላቸው ድንጋጌዎች

የሰው ሃይል አስተዳደር ጥፋቶች (ጉቦ) አንቀጽ 9(4)

በአደራ በተሰጠ ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ አንቀጽ 14(1)(4)

በሥራ አጋጣሚ የሚፈጸም የመውሰድና የመሰወር ወንጀል አንቀጽ 15 (1) (ሀ)

ያለአግባብ ፍቃድ መስጠት ወይም ማጽደቅ አንቀጽ 20(1)

## የሙስና ወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች

❑ **ሕጋዊ፣ ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች (በአንድነት?)**

- **ግዙፋዊ ፍሬ ነገር:-** ድርጊት አልድርጊት
- **ሕጋዊ ፍሬ ነገር፡-** ከልካይና አስቀጪ ሕግ
- **ሞራላዊ ፍሬ ነገር፡-** ሊጨበጥ፣ ሊዳሰስ ሊታይ የማይችል በወንጀል አድራጊ አስተሳሰብ ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡
- በማመሳሰል ወንጀል መፍጠር ፈጽሞ የተከለከለ ነው

{(አንቀጽ 2(2)}

የቀጠለ…

- ❑ **ወደ ሙስና ወንጀሎች ስንመጣ በመርሕ ደረጃ ለየት ያለ ደንብ እናገኛለን።**

**✓ሙከራ እና ፍጻሜ ያገኙ ወንጀሎች**

- የተመድ ጸረ ሙስና ስምምነት (UNCAC)፣ አንቀጽ 27(2) (2)
- *አ/ቁ. 881/2007 መርሕ በአንቀጽ 4(2)፤የጥቅም ትርጉም አንቀጽ 2(13)*

(ለምሳሌ በአዋጁ አንቀጽ 10፣ 11፣ 16፣ 25፣ 26፣ 27፣ 28፣ 29፣ 30 ላይ ጥቅምን ለማግኘት መጠየቅ ወይም ማቅረብ፣ የተስፋ ቃል መናገር ወይም መስጠት፣ ቃል መግባት፣ መስማማት )

see United Nations Handbook on Practical Anti-Corruption Measures for Prosecutors and Investigators, Vienna, September 2004.

- የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት በገንዘብ የሚተመንም የማይተመንም ሊሆን ይችላል። (For instance, Sextortion)

## የቀጠለ…

- ዓቃቤ ሕግ በሙስና ወንጀሎች ላይ በመርሕ ደረጃ ጥቅም የማግኘት ወይም ጉዳት የማድረስ የተከሳሹ የሃሳብ ክፍልን እንዲያስረዳ አይገደድም፡፡

*"ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር የሙስና ወንጀሎቹ የተፈፀሙት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት መሆኑ በተደነገገ ጊዜ በድንጋጌው የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬ ነገር መፈጸሙ ከተረጋገጠ ድርጊቱ የተፈፀመው ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም የሦስተኛ ወገን መብትን ወይም ጥቅምን ለመጉዳት እንደሆነ ይገመታል" አንቀጽ 3*

- ✓ *የወንጀል ሕግ፣ አንቀጽ 3*
- ✓ *ሰበር ሰሚ ችሎት፣*ቅጽ 24፣ ሰ/መ/ቁ162738፣ መጋቢት 30/2012

**ግምት… ለምን**

## የቀጠለ...

1) ***የስሌት ወንጀል ነው፣ የተወሳሰበ ነው።***

2) ***ዓለም አቀፍ ደንብ ነው፣***

- *የተመደ ጸረ ሙስና ስምምነት የሀሳብ ክፍል* ተጨባጭ ከሆኑ እውነታዎች ወይም የሁኔታዎች ክስተት (Objective Factual Circumstances) ይወሰዳል አንቀጽ 28፣ አሜሪካ፣ ሆንግ ኮንግ፣ ሕንድ፣ ፓኪስታን ናይጀርያ

3) ***ለኢትዮጵያም ይህ አዲስ መርሕ አይደለም።***

- በነባሩ 1949 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አ. 641 (3)፣ 628
- በኢፌዲሪ ወንጀል ሕግ አንቀፅ 663 እና 675 (3)
- **ከሙስና ሕግ አንጻር፡-**
  - ✓በልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 13፣
  - ✓በጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/97 አንቀጽ 37 (2)(3)

# የቀጠለ…

✓በኢፌዲሪ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 403

✓የኢፌዲሪ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲውም ተከሳሽ በሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ላይ አደጋ ማድረስ፣ እንደ ሽብርተኝነት፣ ሙስና…

**4) ይህ ግምት 'ሊቀለበስ የሚችል' ('Rebuttable Presumption') ነው።**

○ሁሉም ድንጋጌዎች  የሀሳብ ግምት አይወሰድባቸውም

○ግምት የሚወሰድባቸው

- አንቀጽ 9፣ 18፣ 22፣ 23፣ 24 የማይገባ ጥቅም ለራስ ለማግኘት፣ ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማሰብ
- አንቀጽ 13፣ 14 (2) ፣ 15፣ 17፣ 20፣ 31፣ 32 የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት
- አንቀጽ 10፣ 11፣ 12፣ 16፣ 19፣ 25፣ 26፣ 28፣ 29፣ 30  ጉቦ ወይም ጥቅም መስጠትና መቀበልን

# የቀጠለ…

## ❑ግምት የመውሰድ መርሕ ከፍ የሚልባቸው ድንጋጌዎች፤

- አንቀጽ 13 (6)(8) የምስጢር ኮድን ወይም ቁልፍ ላልተፈቀደለት ሰው አሳልፎ ሰጥቷል በሚል ክስ የቀረበበት ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ
- አንቀጽ 21 (1) (ለ) እና (2) ምንጩ ያልታወቀ ሀብት በማካበት የተከሰሰ ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ
- አንቀጽ 23(4)_ ሀሰተኛ ሰነድ ይዞ የተገኘ ሰራተኛ
- አንቀጽ 31 ከባድ እምነት ማጉደል ወንጀል

# የቀጠለ

- **በቸልተኝነት የሚያስቀጡ ወንጀሎች የሐሳብ ክፍል ማስተባበሉን ወደ ተከሳሽ ይዞራል የሚል መርሕ አይሰራም።**
  - ለምሳሌ የምስጢር ኮድ ወይም ቁልፍ አሳልፎ መስጠት፤ ታሽጎ የተረከበውን እቃ መክፈት፣ መውሰድ፣ በዚህ መገልገል፤
  - በሕገ ወጥ መንገድ የመሰብሰብ ወይም የማስረከብ ስራ፤ ፈቃድ ያላግባብ መስጠት ወይም መፍቀድ፤
  - የስራ ምስጢርን መግለፅ፤
  - መንግሥታዊ ሰነዶችን ማጥፋትና ጉዳት ማድረስ
- **ሆነ ተብለው የሚፈጸሙ ወንጀሎችም ቢሆን ዓቃቤ ሕግ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት**
  - ✓ በኢፌዲሪ የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የዓቃቤያነ ሕግ የአሰራር ማኑዋል፣ አንቀጽ 43(3)፣
  - ✓ ተከሳሹ ማቅረብ የሚችለው ማስረጃ ካለው ማየትና መመርመር አለበት።

## ክፍል ሦስት

## ከበድ ሙስና



# What is Grand corruption

# (Transparency International 2019).

- Grand corruption means the commission of any of the offences in UNCAC Articles 15 - 25 as part of a scheme that

(1) involves a high-level public official; and

(2) results in or is intended to result in a gross misappropriation of public funds or resources, or gross violations of the human rights of a substantial part of the population or of a vulnerable group" (Transparency International 2019).

(de facto or de jure,)

# ከባድ ሙስና/Grave Corruption



# ክፍል አምስት

## የፀረ ሙስና ልዩ የሥነሥርዓትና የማስረጃ ሕግ ድንጋጌዎች

- ሥልጣን /jurisdiction/
- ዋስትና /bail/
- ቅድመ ክስ ዝግጅት /preparatory hearing/
- የወንጀል ተካፋይን ከክስ ነፃ ስማድረግ /immunity from prosecution/
- ልዩ የምርመራ ዘዴዎች
- የጠቋሚዎች ጥበቃ /protection of whistle blowers/



# ጠለፋ/Intercption

**ግንኙነትንና ደብዳቤን ስለመጥለፍ (አንቀጽ 46**

- በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 26/1 እና 2 እንደተደነገገዉ ማንኛዉም ሰዉ በስልክ በፖስታ፣ በቴሌኮሙኒኬሽ ወዘተ ግንኙነት የማድረግ መብት ያለዉና ይኸዉ መብቱ የማይደፈር ስለመሆኑ ተመላክቷል
- ይሁንና ብሔራዊ ደህንነትን ፣የህዝብን ሰላም፣ወንጀልን መከላከል፣ጤናና ህዝብን ሞራል ሁኔታ በመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነጻነት በማስከበር ሲባል መብቱ በህግ ገደብ ሊደረግበት እንደሚችል በህገ መንግስት አንቀጽ 26/እና 3 ከተቀመጠዉ መረዳት ይቻላል፣
- ለሙስና ወንጀል ምርመራ ወይም ማስረጃ ለማሰባሰብ አስፈላጊ ከሆነ በስልክ፣ በቴሌኮሚኒኬሽን ወይም በኤሌክትሮኒከስ፣መሳሪያ፣ በደብዳቤ የሚደረግ ግንኙነት እንዲጠለፍ ሊታዘዝ እንደሚችል በህግ ተፈቅዷል፡፡ (ልዩ ስነስርአት ህግ አንቀጽ 46)

# መወያያ

1. ጉቦ የተጠየቀ ሰዉ ከጉቦ ጠያቂዉ ጋር ያደረገዉን የስልክ ንግግር በራሱ ሞባይል/ በቪዲዮ ካሜራ ቀርፆ ለፖሊስ ሪፖርት አድርገ፣

2. በተመሳሳይ ጉቦ የተጠየቀ ሌላ ሰዉ ለፖሊስ ሪፖርት አድርጎ ንግግሩን እንዲቀርጽ በፖሊስ ሃላፊ ይፈቀድለትና በተሰጠዉ የድምፅ/የምስል ከጉቦ ጠያቂዉ ጋር ያደረገዉን ንግግር ቀርፆ ለፖሊስ ሪፖርት አደረገ

ሁለቱም ጉዳዮች ዐቃቤ ህግ ክስ መስርቷል፣ ይሁንና በዳኞች የተለያዩ አቋም ተይዟል፣

1. የመጀመሪያዉ ዳኛ ሁለተኛዉ አግባብ ባለዉ ሃላፊ የተፈቀደ መሆኑን በመጥቀስ ተቀብለዉ በተከሳሽ ላይ ሲወስኑ በመጀመሪያዉ ክስ በግለሰብ እንዲቀረፅ በህግ ባልተፈቀደለት ሰዉ የተቀረፀ በመሆኑ ዉድቅ ያደረጋሉ፣

2. በሁለቱም ሁኔታ የተገኘዉ ማስረጃ በህግ ያልተከለከለና የተፈቀደም መሆኑን ተቀብለዉ በተከሳሽ ላይ ዉሳኔ ይሰጣሉ፣ የትኛዉን ሃሳብ ይደግፋሉ

# የቀጠለ…

- Consensual Recording

If one party of the activity to be recorded provides consent, then the activity can be intercepted/Recorded without a judicial order.

- Preservation of evidence

thanks

አመሰግናለሁ




# ጥያቄዎች